# ኑሮ በሀዘን

ዝክር ለሣሙዔል ለዘላለም
ሽማህ የፍትህ ነው ካባህ የሰላም፡፡
ሌቱ ለቀን ቢለቅ ክረምትም ለበጋ
ሕዝብ አክብሮትህ ምክርህ ከእኛ ጋ፡፡
በአካል ባትኖር መንፈስህ ግን አለ
ልባችንም ከስሎ ሣሙዔል እያለ
ሀዘን አኮራምቶን ቅስማችን ተሰብሮ
አለንልህ ሣሚ ከተባለ ኑሮ፡፡
እየከበደ እንጂ ሲቀል አላየነው
አለመመለስከን መች ነው የምንለምደው?
ሁለት ዓመት ጊዜ ሁለት መቶ ይመስላል
ካንተ  ተለይቶ መቀጠል ከብዶናል፡፡
ጉጉትህ ለሠላም ለሀገር ፍቅርህ
ትኩስ ነው ሣምዬ ያንተ ትዝታህ፡፡
የአላማ ፅናትክን ለማን አወረስከው
የጀመርካቸውን ማን ሊያጠናቅቅ ነው?
በሞት ድል ተነስተህ መክነህ የቀረኸው፡፡
አልተቀበልን እኛ አላመንም ከቶ
ጉድጓድ መግባትህን ልባችን ዘንግቶ፡፡
ሳቅህ ይሰማናል በተደጋጋሚ
ሁሌም ከእኛ ጋር ነህ አትዘንጋ ሣሚ፡፡
የፍኖት የፍቅር የፅናቱ መሪ
ለሚያውቅህ ሁሉ ለወገንም አኩሪ፡፡
ትክክል ሚዛኑን የማታጋድል
አንተን ማጣት ከቶ አለመታደል፡፡
ናፈቅከን ሣሙዔል ራቀ ድምፅህ
የፍትህ ርትዕ የአንድነት ድምፅህ፡፡
መቼ ለት ሰመረ መች ተጠቃለለ
አንተን ይዞብን ሞት የኮበለለ?
ሻማና ጧፉ ይብራ ለዓላማህ
ለህዝብም አርነት ይስመር ፍታትህ፡፡
ስራህም ድካምህ ለድህው ሰው ብቻ
ታላቅ ሰው የነበርክ ያላገኘህ አቻ፡፡
የማይረሳ ነው በጎ ዓላማህ
ሁሌም የሚናፈቅ ያ አሳሳቅህ፡፡
አልተወገደ ከፊታችን
ደምቆ ይቀመጣል ከልባችን
ይዘዋወራል በደም ስራችን፡፡
በጣም ይመራል የሀዘን ኑሮ
እየተፋጀ ጠዋት ማታ እሮሮ፡፡

ዝም አለ ሣሙዔል ሄደብን በቃ
ቃሉን አክብሮ ምኔም ሳይነቃ፡፡
ቀረብን ለእኛ አጎደለን
ያለውን ከእኛ ያቀፍነውን
እናወራለን ነበር ብለን፡፡

ከቤተሰቦቹ